የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የተያዥ ወይም የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት
መመሪያ ቁጥር 11/2004

ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ባህር ዳር
ጥቢ 2004 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የተያዥ ወይም የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት
መመሪያ ቁጥር 11/2004

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩ አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 ዓ.ም አንቀጽ 67 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

፪ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2004 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፫ ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ቁጥር 178/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ቁጥር ---/2004 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ቢሮው" የሚለው ቃል የሚወክለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮን ነው፡፡
2. "ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት በገንዘብ ሰብሳቢነትና ያዥነት ወይም በንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቀጣሪ ሰው ነው።
3. "ዋስ" ማለት ሠራተኛው በመንግሥት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ወይም ኃላፊነቱን ባግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት ለሚደርሰው ጉድለትና ጥፋት ኃላፊ በመሆን

የጎደለውን እና/ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመተካት በመስማማት የዋስትና መያዣ በመተማመኛነት የሚያቀርብ/የሚያስይዝ ሰው ነው፡፡

4. "የዋስትና መያዣ" ማለት ሠራተኛው ለተሰጠው የመንግስት ሃብትና ንብረት ተጠያቂ ለመሆን ሠራተኛው ራሱ/ዋሱ በመተማመኛነት የሚያቀርባቸው በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታን፣ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን፣ የመኪና ሊብሬን እና የመሳሰሉትን የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ያካትታል፡፡ ሆኖም በደመወዛቸው ዋስትና ዋስ የሚሆኑ ሰዎች የወር ደመወዛቸው 2000/ሁለት ሺህ ብር/ እና ከዚያ በላይ መሆኑንና ከዚህ በፊት በደመወዛቸው ዋስትና ለሌላ ሰው ዋስ ስላለመሆናቸው ከሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የሚያመጡት የጽሑፍ ማስረጃ/የማረጋገጫ ሰነድ እንደዋስትና መያዣተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፬ የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በኣማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 የመንግሥት መስሪያ ቤት ተብለው በተመለከቱት ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭ የመመሪያው ዓላማ

የመንግሥት ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመጠበቅ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ሠራተኞች ጋር በተያያዘ በመንግስት ገንዘብና ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉድለት ወይም ጥፋት ኃላፊነትን በመውሰድ የጠፋውን እና/ወይም የጎደለውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲተካ/እንዲመለስ የሚያስችል የዋስትና ሥርዓት ማቋቋም ነው፡፡

፮ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት

ማንኛውም የመንግሥት መስሪያ ቤት፡-

1. በክልሉ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር እና ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡ፣ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣ አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት

የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ ወይም እንዲያቀርቡ እና ለዋስትናው ውል እንዲይዙ ማድረግ ይኖርበታል።

2. በሠራተኛው ወይም በዋሱ የሚሰጠው የዋስትና መጠን በሠራተኛው ኃላፊነትና ዋስትናው በመቀጠር ችሎታው ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዋስትናው ውል ይወሰናል።
3. ለሠራተኛው የተያዘው ዋስትና እንዲቋረጥ ወይም እንዲቀር የሚያደርጉ ሁኔታዎች አለመፈጠራቸውን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ አለበት።
4. ሠራተኛው ወይም ዋሱ ያቀረበው የዋስትና መያዣ የሚወክለው ንብረት ይገባኛል ባይ የማይቀርብበትና እግድ ያልተጣለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲቀርብ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት።
5. ሠራተኛው ወይም ዋሱ ንብረቱን በዋስትና ለማስያዝ የተስማማበት ውል በሕግ የፀና እንዲሆን የውሉ ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገብ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
6. የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በሕግና በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ ወይም ህግን በሚጥስ መልክ የመንግሥት ገንዘብና ንብረት እንዲባክን ትዕዛዝ ቢሰጥ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

፯ የሠራተኛው ግዴታ

1. በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም በንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚመደብ ማንኛውም ሠራተኛ ዋስትና ማቅረብ አለበት።
2. ማንኛውም የዋስትና መያዣ ዕግድ ያልተጣለበትና ይገባኛል ባይ የማይቀርብበት መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።
3. ሰነዱ ህጋዊ ባይሆን፣ በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ በማስመሰል የተዘጋጀ ሆኖ ቢገኝ በአስተዳደር ከሚወሰደው እርምጃ በተጨማሪ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።
4. በንብረቱ ወይም በደመወዝ ዋስትና ዋስ የሆነ ሰው በዋስትና ያቀረበው ዋስ ዋስትናውን ለማንሳት ወይም ለመሰረዝ ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ሠራተኛው ምትክ ዋስ የማቅረብ ግዴታ አለበት። የቀድሞው ዋስ ጥያቄም በሠራተኛው እጅ ያለ ገንዘብ ወይም ንብረት ተመርምሮ ዕዳ መኖር ወይም አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሠራተኛው ጉድለት ያለበት ከሆነና ሠራተኛው ጉድለቱን ካልሸፈነ ***ከ30 /ሠላሳ/ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ*** ውስጥ ሂሳቡ በመስሪያ ቤቱ የውስጥ አዲት ተመርምሮ እንዲቀርብ በማድረግ፣ ይህንን ጉድለት ዋሱ እንዲሸፍን ተደርጎ ጥያቄው ተፈጻሚ ይሆናል። ሆኖም መስሪያ ቤቱ አስቀድሞ ሠራተኛው ጉድለቱን እንዲሸፍን ሳይጠይቅ በቀጥታ

ዋሱን እንዲከፍል ወይም እንዲመልስ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ተደርጎ ጥያቄው ተፈጸሚ ይሆናል፡፡

5. ሠራተኛው የተረከበውን ማንኛውንም የመንግሥት ንብረት ለተጠቃሚዎች አስፈላጊ አፈጻጸሞችን በማሟላት እስከሚያስረክብ ድረስ ለሚደርሰው ጉዳት፣ ጉድለትና ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡

፲ የዋስ ግዴታ

1. በመንግሥት መስሪያ ቤት ለአንድ ሠራተኛ ዋስ ለመሆን ፈቃደኛ የሚሆን ሰው ንብረት ወይም የመንግስት ደመወዝ ያለውና ንብረቱን ወይም ደመወዙን በዋስትና ለማስያዝ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ረቂቅ በተመለከተው መሠረት ሙሉ ስምምነቱን መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. ሠራተኛው የገንዘብ ጉድለት ቢያደርስ ወይም ይዞ ቢጠፋ፣ ንብረት ቢያጎድል፣ ጉዳት ወይም ብልሽት ቢያደርስ በመንግሥት ሀብት ላይ ለሚደርሰው ማናቸውም ጥፋት ሙሉ ተጠያቂ በመሆን እንደ ጥፋቱ መጠን ያስያዘው ንብረት ተሸጦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
3. ዋሱ ለዋስትና የሚያቀርበው ማናቸውም የዋስትና መያዣ እግድ ያልተጣለበትና ይገባኛል ባይ የማይቀርብበት መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
4. ሠራተኛው/ዋሱ የሚያቀርበው የዋስትና መያዣ በውል ምዝገባና ሰነዶች ማረጋገጫ ጽሕፈት ቤት እንዲመዘገብና የዋስትና ግዴታው እስኪቋረጥ በሚመለከተው መስሪያ ቤት ተከብሮ የሚቆይ እንዲሆን መስማማት አለበት፡፡

፲፩ ዋስትና ሊቋረጥ ወይም ሊቀር የሚችልባቸው ሁኔታዎች

1. ሠራተኛው ከገንዘብ ያዥነት ወይም ገንዘብ ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያገርነት ወይም ጥበቃ ሥራ በመነሳቱ፣ ሥራ በመልቀቁ በእጁ የሚገኘውን የመንግሥት ሀብት ያለምንም ጉድለት ሲያስረክብና ለዚሁም የማረጋገጫ ሰነድ ሲቀበል፣
2. በዋስትና የተያዘው ንብረት ለሌላ ሥራ በመንግሥት ተፈልጎ የዋሱ የባለቤትነት መብት ሲቀር ሲያጣ ሲነፈግ ፣
3. የተያዘው ንብረት በአደጋ ከጠፋ ወይም ተበላሽቶ ዋጋ ካጣ ወይም ንብረቱ ተሰርቆ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አለመገኘቱ በፖሊስ ከተረጋገጠ፣
4. ዋስ የሆነው ሰው ዋስትናው እንዲወርድለት ካመለከተ በአንቀጽ ፮/4 የተመለከተው ሲሟላ፣
5. በዋስትና የተያዘው ንብረት በእርጅና ዋጋውን ካጣ፣

6. ዋሱ ወይም ሠራተኛው ከሞተ እና ሠራተኛው ከመሞቱ በፊት ንብረት ወይም ገንዘብ ያጎደለ ከሆነ ዋሱ በኃላፊነት ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡

፲ የማስታወቅ ወይም የመተካት ግዴታ

1. ሠራተኛው ከገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት፣ ንብረት ያዥነት ወይም ጥበቃ ሥራው ሳይነሳ ዋስትናው በአንቀጽ ፱ /2-6/ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ቢቋረጥ፣ በምትኩ ሌላ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ አለበት፣
2. አሰሪው መስሪያ ቤት የመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ በሌላ መስሪያ ቤት ለሚገኝ ሠራተኛ ዋስትና ገብቶ ከሆነና ሠራተኛው የሚሠራበትን መስሪያ ቤት ከለቀቀ ዋስትና ለሰጠበት መስሪያ ቤት ሥራውን ስለመልቀቁ የማሣወቅ ግዴታ አለበት::

፲፩ ዋስ ማቅረብ ያለመቻል

በተመሳሳይ ደረጃ በዝውውር ለገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት፣ ንብረት ያዥነት ወይም ጥበቃ የሥራ መደብ ላይ እንዲመደብ የተደረገ ወይም ዋስ በማቅረብ ከእነዚህ የሥራ መደቦች ላይ ሲያገለግል ቆይቶ የዋስትናው ውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፱ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተቋረጠ ሠራተኛ ዋስ ወይም ምትክ ዋስ ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን መስሪያ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ ሠራተኛው ያለውን ብቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋስትና እንዲያቀርብ በማይገደድባቸው የሥራ መደቦች ላይ መድቦ ሊያሰራው ይችላል፡፡

13. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት ፩/2004 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

አየነው በላይ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ለመንግስት ሠራተኞች የተሰጠ የዋስትና ውል

ይህ የዋስትና ውል በ..... ከዚህ በኋላ "ዋስትና ተቀባይ" ተብሎ በሚጠራው አድራሻ ..... እና በአቶ/ወሮ/ወ/ት..... ከዚህ በኋላ "ዋስ" ተብሎ በሚጠራው አድራሻ ክ/ከ.....ወረዳ.....የቤት ቁጥር.....ስልክ ቁጥር..... መካከል ዛሬ..... ቀን 200.... ዓ.ም. ..... ከተማ ተደረገ፡፡

አንቀጽ 1

የውሉ መሰረት

ይህ የዋስትና ውል "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር .... /200..." በሚያዘው መሰረት የተዘጋጀ ነው፡፡

አንቀጽ 2

የውሉ ዓላማ

በዚህ ውል አንቀጽ 1 በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት ዋስ በሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኞች በቅጥር ወይም በዝውውር ወይም በዕድገት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ሲመደቡ ዋስ ወይም በሠራተኛው እና በቀጣሪው የመንግስት መስሪያ ቤት መካከል የሚደረግ ውል ሲሆን ሠራተኛው በ..... የሥራ መደብ ተቀጥሮ ሲሰራ ከስራው ጋር በተያያዘ ለተረከበው የመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም የጥበቃ ኃላፊነት ለሚደርሰው ጉድለት እና/ወይም ጥፋት ዋሱ ከሠራተኛው ጋር በተናጠልም ሆነ በጋራ ኃላፊ እንዲሆንና የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲከፍል/እንዲመልስ ለማስቻል ነው፡፡

አንቀጽ 3

የዋሱ መብትና ግዴታዎች

3.1 መብቶቹ

3.1.1 ዋስ ዋስትና የተገባለት ሠራተኛ ላይ ዕምነት ቢያጣ ወይም በሌላ ምክንያት ተያዥነቱ እንዲነሳለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ዋስ የሆነለት ሠራተኛ

ያጎደለው ወይም ያጠፋው ገንዘብ ወይም ንብረት መኖሩ ከተረጋገጠ ግዴታውን ሳይወጣ ዋስትናው ሊቀር አይችልም፡፡

3.1.2 ዋስ የሆነለት ሠራተኛ የተረከበውን ገንዘብ ወይም ንብረት በሙሉ ሲያስረክብ እና ምንም ዕዳ እንደሌለበት በቀጣሪው መስሪያ ቤት ሲረጋገጥ ከግዴታው ነፃ ይሆናል፡፡ የዋስትና ውሉም እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

3.1.3 ዋስ የዋስትና መያዣ የሚወክለው ንብረት የሚያወጣው ዋጋ እንዳለ ሆኖ በዚህ ውል አንቀጽ 4 ከተገለፀው የገንዘብ መጠን ቢበልጥም የዋስ ግዴታ በዚህ አንቀጽ በተገለጸው የገንዘብ መጠን ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

3.2 <u>ግዴታዎቹ</u>

3.2.1 ዋስ ሠራተኛው በተመደበበት የሥራ መደብ ተቀጥሮ ሲሰራ ከሥራው ጋር በተያያዘ በተረከበው ወይም በሚጠብቀው የመንግስት ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉድለት ወይም ጥፋት ዋሱ ከሠራተኛው ጋር በተናጠል እና በጋራ ኃላፊ በመሆን የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመመለስ ወይም ለመተካት ተስማምቷል፡፡

3.2.2 ዋስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2.1 መሠረት የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲከፍል እና/ወይም እንዲተካ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ____ (_____) ቀናት ውስጥ ግዴታውን ካልተወጣ በንዑስ አንቀጽ 3.2.4 በተገለጸው መሠረት በመያዣነት የተሰጠውን ንብረት እንዲሸጥ ተስማምቷል፡፡

3.2.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በደመወዙ ዋስትና ዋስ የሆነ ሰው በንዑስ አንቀጽ 3.2.1 መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ የወር ደመወዙን 1/3 (አንድ ሶስተኛ) ዋስትናው እስኪሟላ ድረስ በየወሩ እየተቀነሰ እንዲከፍል ተስማምቷል፡፡

3.2.4 የጠፋውን ወይም የጎደለውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት መመለስ ወይም መተካት ሳይችል ከቀረ በዋስትና የተሰጠው ንብረት ተሸጦ በዚህ ውል አንቀጽ 4

ከተገለፀው የገንዘብ መጠን ሳይበልጥ በጠፋው/በጎደለው ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ልክ ዕዳውን ለመክፈል ተስማምቷል፡፡

3.2.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2 የተገለጹት የዋስ ግዴታዎች ሠራተኛው ንብረቱን በማስያዝ በሚገባው ዋስትና ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 4

የዋስትናው ገንዘብ መጠን

ዋስ በዚህ ውል መሰረት የሚሰጠው ዋስትና እስከ ብር _____ (_____ብር) ድረስ ይሆናል፡፡ ለዚህም ዋስ/ሠራተኛው _____አስይዟል፡፡

አንቀጽ 5

ተፈጻሚ ሕጎች

ይህ የዋስትና ውል እንደተጠበቀ ሆኖ የዋስው እና ዋስትና ተቀባይ መብቶችና ግዴታዎችን ጨምሮ የክልሉ መንግስት የተያዥ ወይም የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር ___/200__ እና የፍትሐ ብሔር ሕግ የዋስትና ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 6

ውሉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የተያዥ ማጎደር

- ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት (_____)
- አድራሻ

  ክ/ከተማ _____ቀበሌ/ወረዳ _____

  የቤት ቁጥር_____ ስልክ _____
- የሚሰራበት መስሪያ ቤት_____
- የሥራ መስክ _____
- በዋስትና የተረከበው ንብረት/ደመወዝ _____

በዚህ ውል ድንጋጌዎች መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም _____

ፊርማ _____

<u>የተያዥ ባል/ሚስት ማጎደር</u>

- **ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት (_____)**
- **አድራሻ**

  ክ/ከተማ _____ቀበሌ/ወረዳ _____

  የቤት ቁጥር_____ ስልክ _____
- **የሚሰራበት መስሪያ ቤት_____**
- **የሥራ መስክ _____**

በዚህ ውል ባሌ/መስቴ ተያዥ በመሆኑ/ኗ መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም _____

ፊርማ _____

<u>ተያዥ/ዋስ የቀረበለት ሠራተኛ ማጎደር</u>

- **ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት (_____)**
- **አድራሻ**

  ክ/ከተማ _____ቀበሌ/ወረዳ _____

  የቤት ቁጥር_____ ስልክ _____
- **የሥራ ክፍል _____**
- **የሥራ መደብ/ኃላፊነት _____**

<u>ምስክሮች</u>

	ስም	**ፊርማ**
1.	_____	_____
2.	_____	_____
3.	_____	_____

ከዚህ በታች ያለው የፌዴራል ረቂቁ ላይ ብቻ ያለ ነው፡፡ ዋናው ላይ የለም፡፡ ያሰፈልጋል የሚል አስተያየት ሰላለኝ ነው የተውኩት አስተያየት ብትሰጡበት፡፡

ለዋስትና የሚቀርብ የሰነድ ዓይነት

1. **የከተማ ቦታ ካርታና ቤት፣ /የተያዥ ወይም የራሱ የተቀጣሪው ንብረት/፣**
2. **ሁሉን አቀፍ ኢንሹራንስ የተገባለት የመኪና ሊብሬ፣**
3. **ከ..... ብር በላይ ደመወዝ ያላቸው ..... ሠራተኞች ከመ/ቤታቸው የሚያመጡት የማረጋገጫ ሰነድ፣**
4. **ከብር ..... ያላነሰ በማይንቀሳቀስ ሒሣብ ባንክ ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ፣**
5. **ለገንዘብ ወይም ለንብረት ጉድለት ማካካሻ እንዲሆን የተገባ የኢንሹራንስ መድን ሰነድ፣**
6. **ከብር ..... ያላነሰ ካፒታል የሚያንቀሳቅስ የንግድ ፈቃድ፣**

3. የዋስትና ሰነዱ አመዘጋገብ

ለዋስትና የሚቀርቡ የንብረት ባለቤትነት ሰነዶች፡-

1. **የይዞታ ባለቤትነት ካርታ ወይም ደብተር ከሆኑ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር /ማዘጋጃ ቤት/ የተሰጠ፣**
2. **ተሽከርካሪ ከሆነ ከመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጠ፣**
3. **በደመወዛቸው ዋስትና ተያዥ የሚሆኑ ሰዎች ከሚሰሩበት መ/ቤት የሚያመጡት የጽሑፍ ማስረጃ፣**
4. **የመድን ዋስትና ከሆነ መድን ከተገባበት የኢንሹራንስ ኩባንያ የሚሰጥ ሰነድ፣**
5. **በባንክ ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ ካስቀመጠው ባንክ የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ፣**
6. **የንግድ ፈቃድ ከሆነ፣ ፈቃድን ከሰጠው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ መሆን ይገባቸዋል::**